# <u>የሽንገላ  የፖለቲካ ባህል ለአንድ የፖለቲካ ፓርቲ ያለው ጎጅነት</u>
(የዶክተር ዋኒ ቶምቤ ላኮ ምክሮች ለፖለቲከኞቻችን)

ከገረመው ሃይሉ ( ካርቱም ሱዳን )

ዶክተር ዋኒ ቶምቤ ላኮ የጁባ ዩኒቬርስቲ መምህርና ጥቁር  ደቡብ ሱዳናዊ ናቸው፡፡ ዶክተር ዋኒ ሱዳን ቪዥን በተባለው የእንግሊዝኛ ጋዜጣ ላይ ስለ ወቅታዊና አጠቃላይ የአገራቸውና አለማቀፋዊ ፖለቲካዊ ሁኔታዎች በተከታትይ ይጽፋሉ፡፡ ዶክተር ዋኒ የሰሜንን ሆነ የደቡብ ሱዳን አክራሪ የፖለቲከኞችን  አመለካከት አይጋሩም ፡፡ የደቡብ አክራሪዎች ግንጠላን እንደብቸኛ አማራጭ አድርገው ሲያቀነቅኑ፥ የስሜን አክራሪዎች ደግሞ በሃይማኖቱም በምኑም አሳበው በፖለቲካው፥ በኢኮኖሚው እና በማህበራዊ ዘርፍ በደቡብ ሱዳናውያን ላይና በሌላው ሱዳናዊ ላይ  ይደርስ የነበረውን አድልኦ አይተው እንዳላዩ መሆን የሚፈልጉና በነበረው እንዲቀጥል የሚፈልጉ ናቸው ፡፡ ዶክተር ዋኒ ታዲያ አድልዎና በደሉ ከተወገደ "አንድነቷ የተጠበቀች ሱዳን ለሁላችንም ትበጃለች" በማለት የደበቡ አክራሪዎችን ሲጎሽሙ  በነበረው መቀጥል ለሚፈልጉት የሰሜን ፖለቲከኞች ደግሞ ያ ጊዜው የመሸበት ፖለቲካና የታሪክ ጎማን ወደ ኋላ ጉታች  መሆንን ደጋግመው ነግረዋቸዋል ፡፡  እነዚህን የሰሜኑን ሆነ የደቡቡን አክራራሪ የፖለቲካ አመለለካከቶችን ለማምከንም በፖለቲካ ፓርቲዎችና እንቅስቃሴቸው እንዲሁም በአገሪቱ ፈርጀ ብዙ ችግሮች ዙሪያ በተደጋጋሚ ይጽፋሉ፡፡ ይህንም ያንንም ይጎሽማሉ ፡፡ የማህበራዊ ሳይንስ ጠበብት የሆኑት ዶክተር ዋኒ የሶስተኛው አለም በተለይም አፍሪካን ቀስፈው በያዙት ችግሮች በተለይም በፖለቲካው ዙሪያ ደጋግመው በጽሁፎቻቸው ይመላለሳሉ፡፡ ይተቻሉ፡፡ በቆጥቋጭ  ብእራቸው አጥፊውን ወገን  ይሸነቁጣሉ፡፡  እውነቱን ሲነግሩት የኮረኮሩትና ያህል ያሰቃል እንደሚባለው ሁሉ ዶክተር ዋኒ የሚጽፉት ስለ አገርቸው ቢሆንም የኛን የፖለቲካና ፖለቲካኞች ሁኔታም እንደመታዎት ወለል አድርጎ የሚያሳይ በመሆኑ እኔንም የጽሁፎቻቸው ታዳሚያቸው አድርገውኛል፡፡ በመሆኑም ከዶክተር ዋኒ ልንማራቸው ይገባሉ ከምላቸው  ሁለቱን መርጨ በሁለት ተከታታይ ጽሁፎች ለማቅረብ አስቤለሁ ፡፡

እነዚህም

1. የማባበል ወይም የሽንገላ ፖለቲካ ለአንድ የፖለቲካ ድርጅት  የሚኖረው ጎጂነት፥
2. የማሳበብ የፖለቲካ ባህል  ወይም "የእናቴ መቀነት አደናቀፈኝ" አይነት የፖለቲካ ባህል፥

የሚሉት ናቸው ፡፡

አንባቢዎች ልብ ሊሉልኝ የሚገባው  የዶክተር ዋኒ ጽሁፎችን በቀጥታ ቃል በቃል አለመተርጎሜን ይልቁንም ባብዛኛው ሃሳባቸውን መዋሴን ነው፡፡

መልካም ቆይታ

<u>የሽንገላ/ማባበል ፖለቲካ ለአንድ የፖለቲካ ድርጅት የሚኖረው ጎጅነት፥</u>

ይህ ጽሁፍ ዶክተር ዋኒ "Why Political placation is detrimental to a political party" በግርድፉ « የሽንገላ ፖለቲካ ለምን ለአንድ የፖለቲካ ፓርቲ ጎጂ

ነው?» በሚል አርእስት   ኦገስት 14 ቀን 2004፡ ዓ.ም ሱዳን ቪዥን በተባለው የእንግሊዝኛ ጋዜጣ ላይ የጻፉትን የተንተራሰ ነው ::
ዶክተሩ ጽሁፋቸውን የሚጀምሩት

> "የተዋጣላቸው የፖለቲካ ድርጅቶች ያላቸውን የሰው ሃይልና የተለያየ አውቀትና ችሎታ በቅጡ ለይተው የሚያውቁና ይህ እውቀትና ችሎታም ትግሉን የሚያግዝበትን መንገድ በቀልጣፋ የአስራር መንገድ የቀየሱ ናቸው ::" በማለት ነው :: አይይዘውም እነዚህ አይነት የተዋጣላቸው ፓርቲዎች ተላላፊ በሆኑት በፖለቲካ ሽንገላና ማቆላመጥ ባህል ተቀስፈው የተያዙ አይደሉም ይሉናል:: በተጨማሪም ስኬታማ ፓርቲዎች ሃቀኛ አባላትን ለማጭበርበርና ለጥምዘዛ የሚያጋልጥ የፖለቲካ የዘፈቀድ አስራርን እንደማይከተሉ ያስረዳሉ:: ዶክተር ዋኒ ቶምቤ ላኮ የፖለቲካ ድርጅቶች ሊሰሩት የሚችሉትንና አቅማቸውን ማወቅ እንደሚገባቸው ፥ ድርጅቶችና የድርጅት መሪዎች ለአባሎቻቸውና ለህዝባቸው እውነታውንና ተጨባጩን እንጂ አንድም ድክመትን ለመሸፍን አለያም ጊዚያዊ ድጋፍ ለማግኘና ከሌሎች የፖለቲካ ድርጅቶች የተሻሉ መስሎ ለመቅረብ ወደ ሽንገላ ወይም ማባበል መውርድ አንደሌለባቸው ያስምሩበታል:: ይህን ሲያብራሩም የሽንገላ ፖለቲካ ጊዜዊ ድጋፍን ለማግኘት ሲባል የሚቃኝ የማደራጀትና የመቀስቀሻ ስትራቴጂ ነው ይሉናል :: አክለውም "የሽንገላ ፖለቲካ አርቆ አስተዋይነት የጎደለው አደገኛ የፖለቲካ አካሄድ ነው" ይሉታል :: ዶክተር ዋኒ ለተቃዋሚ ፓርቲዎች ሲመክሩም
>
> > የጥቅሱ መጀመሪያ " አገርን መምራት የሚመኙ ፓርቲዎች በማባበል ላይ የተመሰረተ የፖሊቲካ ባህል መገንባት የለባቸውም :: ይህን ካደረጉ በፍጥነት እንደአሸዋ በሚናድ መሰረት ላይ የተገነባና በማንኛውም ወቅት ብዙ የተባለት ድርጅታዊ ጥንካሬ መሰረቱ ተንዶ ወደማያበራ አለመረጋጋት ያመራልና " የጥቅሱ መጨረሻ

ሲሉ እቅጩን ይነግሯቸዋል::

ይህ አባባላቸው አሻግሮ የኛን ቅድመ 1997 ምርጫ ድህረ 1997 ምርጫ የአገራችንን ፖለቲካና የተቃዋሚ ፖለቲከኞችቻንን ሁኔታ በጨረፍታም ቢሆን እንድንቃኝ ያደርገናል:: በቅድመ ምርጫ ስላማዊ ትግል ከሚጠይቃቸው የትግል መርሆዎች እጅግ እርቀው ያለ ምንም ቅድመ ሁኔታና የሃቀኛ ምርጫ መደላድልና መስፈርቶች ባልተሟሉበት ሁኔታ በወያኔ ምርጫ መስፈርት ዙሪያ ሰተት ብለው የገቡትን ሰናገኝ ከምርጨው በኋላ ደግሞ የገቡትን ቃል ሁሉ ክደው የወያኔን ፓርላማ በማሞቅ ላይ ያሉትን የአገራችን የፖለቲካ ድርጅቶችና መሪዎቻቸውን እንድናሰተውል ይገፋፉናል:: የተቃውሞው ጎራ ባንድ ድምጽና በህብረት ወያኔን ወጥሮ የምርጫ ህጉ እንዲሻሻል ፥ በወያኔ ካድሬዎች የተሞላው የሚርጫ ኮሚሽን ፍርሶ ሁሉን ወገን ባቀፈ አካል እንዲተካ ፥ የፖለቲካ እስረኞች እንዲለቀቁ፥ የወያኔ አዳናቂዎች ያልሆኑ ነጻና ገለልተኛ አለማቀፍ የምርጫ ታዛቢዎች እንዲጠሩ ወዘተ የሚሉትን ወቅታዊ ጥያቄዎችን በማንሳት ከመታገል ይልቅ በየፊናቸው ጊዜዊ ድጋፍ ለማግኘት ያደረጉትን እሩጫ ያስታውሰናል:: ከገባቸው ፖለቲከኞቻችን ከግንቦት ምርጫ በኋላስ ብለው አስቀድመው ማማተር እንደነበረባቸው ያመላክታል:: ይህ ማለት ግን ግንቦት 7 ቀን 1997 የተገኘውን ታሪካዊ ድል ለማጣጣል አለመሆኑን ማስገንዘብ እወዳለሁ።

ዶክተር ዋኒ የሽንገላ አካሄድ ሃቀኛ አባላት ለድርጅታቸው ያላቸውን ትስስር፥ የባለቤትነትና የነጻነት ስሜትን በሂደት የሚሸረሽር እንዲሁም ለድርጅቱ ከፍተኛ ጠቀሜታ ባላቸው የተለያዩ ርእሰ ጉዳዮችን አባላቱ ሃላፊነት ወስደው ግልጽ ለማድረግ ያላቸውን ችሎታና ብቃትን የሚጎዳ ነው ይሉታል :: ዶክተር ዋኒ ሃገራዊ ፓርቲ

ሁሉንም በዙሪያው ሊያሰባስብ የሚችልና የሁሉንም አባላቱን አመኔታና አክብሮት ያተረፈ ርእዮት መፍጠር አለበት ይሉናል ። አንድ ድርጅት አባላቱን ባለማክበር አባላትን ከገንቢ የፖለቲካ ተግባራት የሚያርቅበት ብዙ መንገዶች እንዳሉ ይነግሩናል። ዶክተሩ አክለውም ፓርቲዎች ለተለያዩ ተቋማት ፥ ለተለያዩ አካባቢዎችና ለተለያዩ ስራዎች ፓርቲውን እንዲወክሉ አባላቱን በሚመድቡበት ወቅት የሚመደቡት አባላት በታወቁ መመዘኛዎች መሰረት ተመርጠው የተመደቡ መሆን እንደሚጠበቅባቸው ያሰምሩበታል። ከዚህ በተጻራሪ ግን ተጨባጭነት በሌላቸው እንዲያውም እውነታን አጣመው በቀረቡ የፖሊቲካ መመዘኛዎችና ብቃት ያላቸውን ለማግለልና ታማኞችን ለመሾም ተብሎ የተቃኘ መሆን እንደሌለበት ያስገነዝቡናል። አንዳንድ የፖለቲካ ድርጅቶች “ድርጅታዊ አሰራር” በሚል ሽፋን ለምና እንዴት ብለው የሚጠይቁ አባሎቻቸውን ከወሳኝ ቦታዎች ለማግለል የሚጠቀሙበትን ጊዜው ያለፈበት ኮሚኒስታዊ አሰራር ልብ እንድንለው ይጋብዙናል። ይልቁንም ይህ ለድርጅታዊ ስራ የሚመደቡ ሰዎችን አንድም በሽፍንሽን አለያም በዘፈቀደ መመደብ ድርጅቱ የራሱን አባላት እንደፖለቲካ ነስብ መቁጠር ነው ይሉታል ። አያይዘውም የፖለቲካ አዋቂዎችን እንደ ፖለቲካ ጨቅላዎች ወይም ነሲቦች መቁጠር በፖለቲካውም ሆነ በሰዎች ስነልቦና ላይ ጥቃትም ንቀትም መፈጸም መሆኑን በመግለጽ ይህን በመፈጸም ራሳቸውንም ሆነ ቆምንለት የሚሉትን አላማ ለሚጎዱት የፖለቲካ ድርጅቶችና የፖለቲካ መሪዎች ሳይደብቁ ይመክራሉ። ለኛም እውንቱን ያፈርጡልናል። ዶክተር ዋኒ ይህን አይነቱን አሰራር በአባሎቻቸው ላይ የሚፈጽሙትን ድርጅቶች ወይም መሪዎች ክህደት እንደፈጸሙ አድርገው እንደሚቆጥሩም አይደብቁም ። በተለይም ይህ ክህደት በአንድ ድርጅት ውሰጥ ቃል ኪዳናቸውንና እምነታቸው በሰጧቸው በጓዶቻቸውና በስራ ባልደረቦች ሲፈጽም ፥ አልፎም ሰዎች በሃሰትና በእውሸት መካከል ያለውን ልዩነት መለየት እንደማይችሉ የፖለቲካ ነሲቦች አድርጎ መቁጠር የበለጠ ስድብ መሆኑን ይነግሩናል ። ዶክተር ዋኒ ቶምቤ ላኮ ፓርቲዎች ስልጣን ከማያዛቸው በፊት በአባሎቻቸው ላይ የሚፈጽሙት ስልጣን ላይ ቢዎጡ በሃገር ላይ ሊፈጽሙ የሚችሉት ነጽብራቅ ነው ሲሉም ያስጠነቅቃሉ ። ቢመረንም ጎምዛዛውን የአብዛኞችን የአገራችንን የፖለቲካ ድርጅቶች አሰራር ቅልብጭ አድርገው ይነግሩናል።

ዶክተር ዋኒ በመቀጠልም አገርን ለመምራት የሚመኙም ሆነ አገርን እየመሩ ያሉ ፓርቲዎች አገር የመምራትና የመገንባት ብቃታቸውን በውስጣቸው ውህደትንና አንድነትን በማስፈን ማስመከር እንዳለባቸው ያሰምሩበታል ። ለአንድ ፓርቲ የተወሰኑ አባላትን ከትምህርትና ከልምድ እውቀታቸው ውጭ ሁሌም በሚያውቁትም በማያውቅትም እርእስ ላይ የክብር እንግዳ የሚያደርግ ነገር ግን ሌሎች በልምድም ሆነ በትምህርት የተሻለ ልምድ ያላቸውን የሚያገል የፖለቲካ ባህል እጅግ አደገኛ እንደሆነ አዙረው ለፖለቲካኖቹ ይመክራሉ ። ዶክተር ዋኒ አክለውም በተለይም በአቀራረባቸው አሰልቺና ስለሚናገሩት ነገር በቂ እውቀት የሌላቸውን ለፓርቲው መተኪያ እንደ ሌላቸው አድርጎ ማየትና ማቅረብ፥ ለፓርቲው ክስረት ነው ይሉናል። ዶክተር ዋኒ በሶስተኛው አለም የፖለቲካ ውድቀት ለመቀጠሉ ዋናው ምክንያትም ብቃት ያላቸው ዜጎች በወሳኝ የስልጣን ቦታዎች አለመቀመጥና ከፖለቲካ ተሳትፎ የማግለል ክፉ የፖለቲካ ባህል መሆኑን ያሰምሩበታል። የዚህን መሰረት ሲያብራሩም ስልጣን ላይ ቢወጡ ወደ ፊት በህዝብና በአገር ላይ ከፍተኛ ሚና በሚኖረው የፖሊቲካ ፓርቲዎች ፕሮግራምን በመቅረጽና በመገምገም ሂደት ላይ ህዝብ እንዲሳተፉ ባለመፈቀዱ ነው ይላሉ ። በመሆኑም ህዝብ መስረተ ሰፊና ውጤታማ ፓርቲዎችን ለመግንባት አላስፈላጊ የፖለቲካ ባህሎችን አሽቀንጥሮ መጣል መጀመር እንዳለበት ዶክተር ዋኒ ያስረዳሉ።

መሰረተ ሰፊና ውጤታማ ፓርቲዎችን መገንባት የሚጀምረው ደግሞ ድርጅቱን በማስተካል፥ የአባላትን ብቃት በመገምገምና በመሳሰሉት ወሳኝ ድርጅታዊ ጉዳዮች ላይ ሁሉም የሚመለከታቸው አባላት የሚሳተፉበት ግልጽ ውይይቶች በማድረግ መሆኑን

ይነግሩናል። ዶክተር ዋኒ አክለውም  ውሳኔዎች በሚወሰኑበት ወቅት በእድሜቸውና በፖለቲካው  የበሰሉ ሰዎች ጥምዘዛናና ሽንገላን እንደማይቀበሉ በመግለጽ ሁሌም የተወሰኑ ክፍሎችን የማያሳትፍና የፓርቲ  ፖለቲካ የተውሰኑ ሰዎች ጉዳይ ሆኖ መታየት እንደሌለበት፥ ማለትም የፓርቲ የፖለቲካ ስራ የተወሰ ቡድን ወይም ግለሰቦች የግል ጉዳይ ሆኖ መታየት እንደሌለበት  በማስረዳት ይህ አባላትን ሆነ የተወሰኑ ክፍሎችን የሚያገል አሰራር መወገድ እንዳለበት ይመክራሉ ።

ይህ የሽንገላ ፖለቲካ ሃቀኛ አባላት ለድርጅታቸው ያላቸውን ትስስር፥የባለቤትነትና የነጻነት ስሜት የሚሸረሽር እንዲሁም ለድርጅቱ ከፍተኛ ጠቀሜታ ያላቸው የተለያዩ ጉዳዮችን ግልጽ ለማድረግ ያላቸውን  ችሎታና ብቃትን  የሚፈታተንና የሚጎዳ መሆኑን ያስረዳሉ ። እንደ  ሱዳናዊው ዶክተር  ሁሉንም በዙሪያው ሊያሰባስብ የሚችል ሃገራዊ ፓርቲ የሁሉንም አባላቱን አመኔታና አክብሮት ያተረፈ ራእይ መፍጠር አለበት። አንድ ድርጅት ለአባላቱ ተገቢውን ትኩረትና ክብደት ባለመስጠት አባላትን ከገንቢ የፖለቲካ ተግባራት የሚያርቅባቸው አያሌ  መንገዶች መኖራቸውን በመግለጽ የፖለቲካ ፓርቲዎችና አባላት ገቺና ገዳቢ ፖሊስዎችን ለመለወጥ በጣም መጣር እንዳለባቸው ዶክተሩ  ይመክራሉ። ይህ አዳዲስ አሰራርና ሃሳብ ለመቀበል አእምሮቻቸውን ለዘጉ ፖለቲከኞቻችን ጥሩ ምክር ነው።

አንድ ፓርቲ ወይም የፖለቲካ ድርጅት  የተለያዩ ብቃትና ችሎታ ያላቸው  አባላትን ያቀፈ መሆኑን በመግለጽ  ፓርቲው ያሉትን አባላት ብቃትና ችሎታ በቅጡ የሚያውቅበት መንገድ ሊኖረው ይገባል ይላሉ ። ፓርቲ ከመፈክር  አንጋቢዎች እስከ ፈር ቀዳጅ ሃሳብ አፍላቂ አዋቂዎች የተሰባሰቡበት ቢሆንም ወደ አባላት መብት ሲመጣ ግን ያላቸው ተሳትፎና የሚሰጣቸው ክብደት ቢለያይም ሁሉም አይነት አባላት በድርጅቱ መዋቅሮች እኩል መደመጥና መስተናገድ እንዳለባቸው  ይመክራሉ ። አንድ ድርጅት ለአባላት ምልመላ በሚሰናዳበትም  ወቅት “ጅብ የማያውቁት አገር ሄዶ ቁርበት አንጥፉልኝ ይላል” እንደሚባለው አይነት መሆን እንደሌለበት በመምከር ይልቁንም አዲስ አባላት የሚቀላቀሉት ነባር አባላትን ፓርቲው እንዴት እንዳስናገዳቸው ግምግመውና አይተው በመሆኑ መጀመሪያ ያቀፋቸው አባላቱ ጋር የሰመረ ግንኙነትመፍጠር እንዳለበት ያስረዳሉ።

በመጨረሻም የፓርቲ መሪዎች  ምንም የማይሳናቸውና ከነሱ ሌላ ድርጅቱና አገሪቱ ሰው እንደሌላት ሆነው መቅረብ እንደሌለባቸው ያስተምራሉ። አገርንም ድርጅትንም ከየትኛውም የውጭ ጣልቃገብነትና የማስፈራራት ልፈፋ በበለጠ እየጎዳ ያለው ይህ የነሱ ግትርነንትና ከኛ በላይ ላሳር የሚለው አመለካከታቸው እንደሆነ ያሰምሩበታል ።

ወደ አገራችን ፊታችንን አዙረን እያንዳንዱን  ነባር  ሆነ በቅርቡ የተመሰረተ  የፖለቲካ ድርጅት ብናስተውል እፍኝ የማይሞሉ ፖለቲከኞች ገነው የወጡበትን አሳዛኝ ክስተት ያስታወስናል። ይህም በተራው አማራጭ ሃሳብ እንዳይፈልቅ ቢፈልቅም እንዲቀጭና እንዲመክን ከፍተኛውን ሚና በመጫዎት  የእድገት እንቅፋት መሆኑን ይነግረናል። ይህ የአዲሶቹ ሆኑ የነባር የፖለቲካ መሪዎቻችን ከኔ በላይ ላሳር ለተቃዋሚ ድርጅቶች ህብረቶች መፍረስና ለትግሉም ወደፊት አንድ እርምጃ አለመግፋት አንዱ ምክንያት መሆኑን የደቡብ ሱዳናዊ ዶክተር  ያስተምሩናል።

በሉ በሚቀጥለው ዶክተር ዋኒ “ስበበኛ ፖለቲከኞችን ” በተመለከተ የሚሉትን  ይዤ እስከምቀርብ ቸር ይግጠምን።

ኢትዮጵያችንን እግዜር ይጠብቃት !